# የላቀ ቁጠባ ለተሻለ ኢንቨስትመንት

ስሜነህ 02-23-17

እ.ኤ.አ. በ2000 የኬንያ ኢኮኖሚ የ14 ቢሊዮን ዶላር ዓመታዊ የጠቅላላ ምርት ዕድገት እንደነበር ከአለም አቀፉ የገንዘብ ድርጅት የወጡ መረጃዎች ያመለክታሉ፤ አያይዘውም የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ በግማሽ ያህል ከኬንያ መቀነሱን ማለትም በስምንት ቢሊዮን ዶላር ገደማ ይከተል እንደነበር በንጽጽር ይገልጻሉ፡፡ ይህ ሰፊ ልዩነት የነበረው ታሪክ መቀየሩን ደግሞ ከሰሞኑ የወጡ እና በመውጣት ላይ የሚገኙ መረጃዎች ያመለክታሉ። የዚህ ተረክ አቢይ ይዘትም ይኸው ነው።

ትዊተርን ጨምሮ በሌሎች ማኅበራዊ ድረ-ገጾች መነጋገሪያ ሆነው ከነበሩ ሰሞንኛ ርዕሰ ጉዳዮች መካከል ዋና የነበረው ኢትዮጵያ የምሥራቅ አፍሪካ የኢኮኖሚ ልዕለ ኃያልነቱን ከኬንያ እየተረከበች መምጣቷን የተመለከተው ነው፡፡ የዓለም የገንዘብ ድርጅትን ዋቢ ያደረጉ ዘገባዎች እንደሚያትቱት፣ በወቅቱ የገበያ ዋጋና ምንዛሪ ስሌት መሠረት፣ ከጠቅላላ የአገር ውስጥ ምርት (ጂዲፒ) ወይም የአገር ኢኮኖሚ አጠቃላይ እንቅስቃሴ በሚለካበት መመዘኛ መሠረት፣ በዚህ ዓመት የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ 70 ቢሊዮን ዶላር ገደማ የሚገመት ግዝፈት ይኖረዋል፡፡ ይህ ካቻምና ከነበረበት 62 ቢሊዮን ዶላር ገደማ አኳያ ሲታይ የስምንት ቢሊዮን ዶላር ዕድገት የታየበት ነው፡፡ በአንፃሩ ኬንያ ካቻምና ከነበራት የ64 ቢሊዮን ዶላር ገደማ ኢኮኖሚ ወደ 69 ቢሊዮን ዶላር የምታሻቅብ በመሆኑ፣ በኢትዮጵያ በስላሽ ተቀድማ አውራነቱን እንደምታስረክብ ይጠበቃል፡፡

በመንግሥት የሚካሄደው ኢንቨስትመንት፣ ከጠቅላላ የአገር ውስጥ ምርት አኳያ የ40 በመቶ ድርሻ እንዳለው የሚያመለክቱት መረጃዎች ይህ ከስምንት ዓመት በፊት ከነበረው አኳያ በእጥፍ እየጨመረ መምጣቱንም ይጠቅሳሉ፡፡ እነዚህ መረጃዎች ሲቀጥሉም በባቡር መስመር ዝርጋታ፣ በኢነርጂ፣ በኢንዱስትሪ ፓርኮች ግንባታና በሌሎችም የመሰረተ አውታሮች የመንግሥት ሚና ገዝፎ የሚታይበት የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ ወደፊትም በዚሁ አኳኋን እንደሚቀጥል የገመቱበትን ምክንያታዊ መረጃዎች ይዘረዝራሉ፡፡ በአንፃሩ የኬንያ መንግሥት በኢኮኖሚው ውስጥ የሚያካሂደው ኢንቨስትመንት በ22 በመቶ እንደሚያድግ ሲጠበቅ፣ ዓመታዊው የአገሪቱ ኢኮኖሚያዊ ዕድገትም በስድስት በመቶ እያደገ እንደሚገኝ

የኬንያ መገናኛ አውታሮች ዘግበዋል፡፡ በኬንያ ዋና ዋና የዜና አውታሮች ሽፋን የተሰጠው የኢትዮጵያ የኢኮኖሚ ዕድገት፣ የአፍሪካ ኢኮኖሚ ልማትና ዕቅድ ኢንስቲትዩትንም አካቷል፡፡ ኢንስቲትዩቱ በድረ-ገጹ እንዳሰፈረው ከሆነ ኢትዮጵያ ለዓመታት በኬንያ የበላይነት ተይዞ የቆየውን የምሥራቅ አፍሪካ የኢኮኖሚ የበላይነት ለመውሰድ ተቃርባለች፡፡

እንዲህ የነበረው የሁለቱ አገሮች የኢኮኖሚ ዕድገት ልዩነት በተለይ ባለፉት አምስት ዓመታት ውስጥ እየጠበበ መጥቶ፣ ጭራሽንም ኢትዮጵያ በተያዘው ዓመት ኬንያን መብለጥ እንደምትጀምር ይፋ የሆኑት መረጃዎች ሁሉ አረጋግጠዋል፡፡ የአፍሪካ ልማት ባንክን ጨምሮ ሌሎች አኀጉራዊና ዓለም አቀፋዊ ተቋማት የሚሳተፉበት፣ ዓመታዊው የአፍሪካ ኢኮኖሚ እንቅስቃሴና ዕድገትን የሚቃኘው ሪፖርትን መሠረት ያደረጉ ትንበያዎች እንዳረጋገጡት ከሆነ ደግሞ ዘንድሮ ኢትዮጵያ የሚኖራት የኢኮኖሚ ደረጃ በምሥራቅ አፍሪካ የበላይ እንድትሆን የሚያበቃት ነው፡፡ በዚህም የበላይነቱን ከኬንያ ለመረከብ ያስችላታል ፡፡

የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ ከጊዜ ወደ ጊዜ እያየለ፣ ዕድገቱም እየጨመረ መምጣቱ በመላው ዓለም የመገናኛ አውታሮች እየተነገረ ነው፡፡ በያመቱ በአማካይ የአሥር በመቶ ዓመታዊ ኢኮኖሚ ዕድገት እያስመዘገበ የመጣው የአገሪቱ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ፣ በምሥራቅ አፍሪካ በኬንያ የተያዘውን የበላይነት ጠብቆ እንደሚዘልቅም ተነግሮለታል፡፡ ለኢትዮጵያ የኢኮኖሚ ዕድገት ከባዱን ሚዛን የያዘው የመንግሥት ድርሻ ነው፡፡ መንግሥት የሚያከናውናቸው የመሠረተ ልማት ግንባታዎች ዋናውን ድርሻ ይይዛሉ፡፡ በመቀጠል ሊጠቀስ የሚችለው በየጊዜው እየጨመረ የመጣው የውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንት መጠን ነው፡፡

100 ሚሊዮን የሚገመተው የኢትዮጵያ ሕዝብ ብዛት 50 ሚሊዮን ግድም ከሚሆነው የኬንያ ሕዝብ ብዛት አኳያ ሲታይ ከእጥፍ በላይ ነው፡፡ የኢትዮጵያ ሕዝብ ይህን ያህል መሆኑ የውጭ ኩባንያዎችን በመሳብ በኩል ወሳኝ ሚና ተጫውቷል፡፡ ለውጭ ገበያ የሚመረቱ ፕሮጀክቶች ላይ መንግሥት የሚሰጠው ማበረታቻና የኢንቨስትመንት ድጋፍም በተመሳሳይ። በዚህም በየአመቱ በቢሊዮን ዶላር የሚገመቱ የውጭ ኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች ወደ አገሪቱ እየመጡ እንደሆነ የዓለም ባንክ መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡

የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን ሰሞኑን ለመገናኛ ብዙኃን ይፋ ባደረገው መረጃ መሠረት፣ በግማሽ ዓመቱ ውስጥ 1.2 ቢሊዮን ዶላር ያስመዘገቡ የውጭ ኢንቨስትመንቶች መጥተዋል፤ ይህም ኢትዮጵያን በምሥራቅ አፍሪካ የኢኮኖሚ የበላይነትን እንድትይዝ እያስቻሏት ከሚገኙ መገለጫዎች ውስጥ ቢመደብም፣ አገሪቱ መሳብ ከምትችለው የውጭ ኢንቨስትመንት ውስጥ አሁንም አነስተኛውን መጠን እያገኘች እንደምትገኝ ገልጿል፡፡

ከውጭ ኢንቨስትመንት ቀጥሎ በሃገሪቱ ኢኮኖሚ ላይ ከፍተኛ ለውጥ በማምጣት፤ ለውጭ ምንዛሬ ግኝት ከፍተኛ ሚና የነበረው የህብረት ስራ ማህበራት አደረጃጀት ነው። በተለይ ማህበራቱ የአገሪቷ ዋነኛ የእድገት ምንጭ የሆነውን የግብርና ልማት በማዘመንና የውጭ ምንዛሪን በማሳደግ በኩል የላቀ ድርሻ እንደነበራቸው የሚያመለክቱት መረጃዎች፤ የዜጎችን የልማት ተሳትፎና ፍትሃዊ ተጠቃሚነትን በማረጋገጥ፣ በሀገሪቱ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ልማት ግንባታ ውስጥ ጉልህ አስተዋፅኦ እያበረከቱ መሆናቸውን ጠቅሰዋል።

በተለያዩ ጊዜያት በስፋት እንደተገለፀው፣ በራስ አቅም ለምናካሂዳቸው ሜጋ ፕሮጀክቶች የፋይናንስ ምንጭ በመሆን ከሚያገለግሉ ተቋማት መካከል የኅብረት ስራ ማህበራት ተጠቃሽ ናቸው። በመሆኑም በውጭ ምንዛሪ ግብይት የተሰማሩ የህብረት ስራ ማህበራት የአባሎቻቸውን ገቢ ለማሳደግና የሀገራችንን የውጭ ምንዛሪ ክፍተት በመሙላት ረገድ ሚናቸው የጎላ መሆኑን ለመገመት አይከብድም።

የግብርና ልማት ስትራቴጂው የፈጠረውን ገበያ ተኮር ምርትና ምርታማነትን በማሻሻል ከአገር ውስጥ ፍጆታ ባለፈ በጥራት፣ በዓይነትና በብዛት በማምረት የዓለም ገበያን ሰብሮ የሚገባ አቅም እየተገነባ የሚገኘው በነዚሁ ማህበራት በኩል ነው።

በሀገር ውስጥ ላለው ኢንዱስትሪ የግብርና ምርቶችን በብዛትና በጥራት በመመገብ ቀጣይነቱን የማረጋገጥና ከግብርና መር ኢኮኖሚ ዕድገት አቅጣጫ ወደ እጅግ ከፍተኛ ኢንዱስትሪ መር ዕድገት ሽግግር ለሚደረገው እንቅስቃሴ በግብይት ስርዓቱ ውስጥ የላቀ ሚና ኖሯቸው የተገኙትም የህብረት ስራ ማህበራት ናቸው።

ባለፉት ዓመታት ከ15 ሚሊዮን በላይ አባላትን ያፈሩ ከ78 ሺህ በላይ መሰረታዊ የህብረት ስራ ማህበራት፣ 373 ዩኒየኖችና አራት የህብረት ስራ ፌዴሬሽኖችን በመላ ሀገሪቱ ማፍራት የተቻለ መሆኑን የሚገልጹት መረጃዎች፤ እነዚህ ተቋማት 17 ነጥብ 6 ቢሊዮን ብር

ካፒታል በማፍራትና ከ10 ነጥብ 2 ቢሊዮን ብር በላይ ቁጠባ በማሰባሰብ የአባሎቻቸውን ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ ከመስራታቸውም ባሻገር በሀገሪቱ እየተመዘገበ ባለው ፈጣን የኢኮኖሚ እድገት የድርሻቸውን በማበርከት ላይ ይገኛሉ።

በግብርና ምርቶች ላይ እሴት በመጨመርና በወጪ ምርቶች ግብይት በመሳተፍ የሀገሪቱን ምርቶች በማስተዋወቅ ለሀገር ገፅታ ግንባታ የድርሻቸውን እየተወጡ ነው። በሁለተኛው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ዘመን የህብረት ስራ ማህበራትን ማደራጀትና ማጠናከር፣ የላቀ ቁጠባ ለኢንቨስትመንት፣ የግብይት ድርሻ ማሳደግና ደህንነታቸውን መጠበቅ ለበለጠ ስኬት ያበቃል።

በሁለተኛው የእድገትና ትራንስፎርሜሽን እቅድ ዘመን በመላ ሀገሪቱ የኅብረት ሥራ ማህበራትን በማጠናከር ረገድ የካፒታል መጠናቸውን ከ12 ነጥብ 3 ቢሊዮን ብር ወደ 26 ነጥብ 3 ቢሊየን ብር ለማድረስ በመንግስት በኩል ግብ ተይዟል። የሴቶችን 50 በመቶና የወጣቶችን 30 በመቶ በላይ የአባልነት ተሳትፎ ለማሳደግም እየተሰራ ሲሆን፤ ከስራ እድል አንፃርም 2 ነጥብ 6 ሚሊየን ለሚሆኑ ዜጎች የስራ እድል ለመፍጠር እንደታሰበም ከኤጀንሲው የወጡ መረጃዎች ያመለክታሉ። የቁጠባ መጠናቸው ያደገና ኑሮአቸው የተሻሻለ አባላት ቁጠባ መጠን ከ6 ነጥብ 6 ቢሊዮን ብር ወደ 20 ነጠብ 5 ቢሊዮን ብር ለማድረስ ጥረት ይደረጋል። የብድር አቅርቦቱን መጠን ወደ 23 ቢሊዮን ብር ለማሳደግ ታልሟል። ዋና ዋና የግብርና ምርቶችን የኤክስፖርት የግብይት ድርሻን ከ7 በመቶ ወደ 40 በመቶ ከፍ ማድረግና 603 ነጥብ 5 ሚሊዮን የአሜሪካ ዶላር የውጭ ምንዛሬ ማስገኘት ከወጡት መረጃዎች መካከል ይገኛል።

በዚሁ መረጃ መሰረት እሴት የሚጨምሩ የተለያዩ ኢንዱስትሪዎች ግንባታ የእቅዱ አካል ተደርጓል። በዚህ በኩል ከሚሰሩ ስራዎች መካከል የወተትና የወተት ተዋጽኦ ማቀነባበሪያ ግንባታ በአምስት ዩኒየኖችና 400 መሰረታዊ ኅብረት ሥራ ማህበራት፣ በሌሎች የግብርና ምርቶች ማቀነባበሪያዎች ግንባታም 100 ዩኒየኖችና 2 ሺህ መሰረታዊ ኅብረት ሥራ ማህበራት የማደራጀት ስራዎች ይከናወናሉ ተብሎ ይጠበቃል። የኅብረት ስራ ማህበራትን የመሰረተ ልማቶች ግንባታዎችን ለማስፋፋት 2ሺ 150 መጋዘኖች፣ 260 ማቀዝቀዣ

መጋዘኖች፣ 7 ትላልቅ የገበያ ማዕከሎች፣ እንዲሁም 110 መካከለኛ የምርት ማሳያና መሸጫ ማዕከላት ይገነባሉ።

እነዚህ በሙሉ እንግዲህ የሃገሪቱ ኢኮኖሚ በዚህ ደረጃ ላይ ስለመድረሱ ከላይ የተመለከቱ አለምአቀፍ ዘገባዎች የህብረት ስራ ማህበራትም የነበራቸው ድርሻ ከፍተኛ መሆኑን የሚያመላክቱ ናቸውና አሁንም ተጠናክረው ሊቀጥሉ ይገባል።